የኢትዮጵያ ፌደራላዊዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፱ ቀን
፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.59
ADDIS ABABA, 27th April , 2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፱/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለአፍሪካ የንግድ ኢንሹራንስ ኤጀንሲ የአባልነት ክፍያ እንዲውል ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ---------------ገጽ ፹ሺ፱፻፷

## CONTENT

PROCLAMATION NO. 939/2016

African Development Fund Financing Agreement for Regional African Trade Insurance Agency Country Membership Programme Ratification Proclamation------------------page 8960

**አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፱/፪ሺ፰ ዓ.ም**

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለአፍሪካ የንግድ ኢንሹራንስ ኤጀንሲ የአባልነት ክፍያ የሚውል መጠኑ ፬ ሚሊዮን ፱፻፸ ሺ ዩ.ኤ( አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

PROCLAMATION NO. 939/2016

**<u>A PROCLAMATION TO FATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND AFRICAN DEVELOPMENT FUND</u>**

**WHEREAS**, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 4,970,000 U.A (four million nine hundred seventy thousand units of Account) for financing Regional African Trade Insurance Agency Country Membership Programme was singed in Addis Ababa on the 30th day of November, 2015;

**WHEREAS,** the House of Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 5th day of April, 2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is here by proclaimed as follows:

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአፍሪካ የንግድ ኢንሹራንስ ኤጀንሲ የአባልነት ክፍያ እንዲውል ከአፍሪካ ልማት ፈንድ የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፴፱/፪ሺ፰ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፴ ቀን ፪ሺ፲፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 2100150033952 የብድር ስምምነት ፀድቋል።

3. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘው ፬ ሚሊዮን ፱፻፸ ሺ ዩ.ኤ (አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

4. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as the ″African Development Fund Financing Agreement for Regional African Trade Insurance Agency Country Membership Programme Ratification Proclamation No. 939/2016.

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 2100150033952 singed in Addis Ababa on the 30th day of November, 2015 between the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and African Development Fund is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount 4,970,000 U.A (four million nine hundred seventy thousand units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 27th day of ,2016**

**MULATU TECHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**